Hallo
Basel-Stadt

Kanton Basel-Stadt

# ተንቀሳቃሽነት

ባቡር፣ አውቶቡስ እና ትራም
በብስክሌት / በእግር
መኪና / ሞተር ሳይክል
የመንጃ ፍቃድ

# ባቡር፣ አውቶቡስ እና ትራም

በስዊዘርላንድ ውስጥ የህዝብ ትራንስፖርት በጣም የዳበረ ነው። እያንዳንዱ ትንሽ ከተማ በባቡር፣ በአውቶቡስ ወይም በትራም ተደራሽ ነው። የትራንስፖርት መጓጓዣዎቹ ሰዓታቸውን ጠብቀው በተወሰነ የጊዜ ልዩነት አገልግሎት ይሰጣሉ።

## የሕዝብ ማመላለሺያ ትራንስፖርት

የህዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት (ÖV) በስዊዘርላንድ ውስጥ ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል። አብዛኛውን ጊዜ በየሰዓቱ መድረስ ስለሚችሉ፣ በሁሉም ከተማ ያሉ ተጓዦች በባቡር፣ በአውቶቡስ ወይም በትራም ይጠቀማሉ፡፡ ጉዞዎቹ በአንጻራዊ ሁኔታ ውድ ቢሆኑም ገንዘብን ለመቆጠብ ብዙ አማራጮች አሉ። ስለዚህ የደንበኝነት ትኬት ወይም የቅናሽ ካርድ መግዛት ያዋጣል። በአንፃራዊነት ርካሽ በሆነው የግማሽ ታሪፍ ደንበኝነት ምዝገባ ካርድ (Halbtaxabonnement) ለምሳሌ በስዊዘርላንድ ውስጥ በየትኛውም ቦታ ግማሹን ይከፍላሉ ።

## ቲኬቶች እና የደምበኛ የውል ቲኬቶች

ባቡር ለመጠቀም የሚፈልግ፣ ከመጓዙ በፊት የመሳፈሪያ ትኬት (Billett) መግዛት አለበት። ቲኬቶች በባቡር ላይ መግዛት አይቻልም። ይህ በአውቶቡሶች እና በትራም ውስጥ በተለየ መንገድ ነው የሚተገበረው። በእያንዳንዱ የSBB ጣቢያ እና በአብዛኛዎቹ የአውቶቡስ ማቆሚያዎች የቲኬት ማሽኖች አሉ፣ እና በትላልቅ የባቡር ጣቢያዎችም ትኬት መሸጫ መስኮቶች አሉ። ቲኬቶችንም በመስመር ኦን ላይን ወይም በተንቀሳቃሽ ስልክ ሊገዙ ይችላሉ።

ብዙ ለሚጓዙ ሰዎች የተለያዩ የደምበኛ የኮንትራት ካርዶች አሉ። እነዚህ ለአንድ ጉዞ ብቻ፣ ለተወሰኑ መንገዶች፣ ወይም ለመላው የስዊስ ትራንስፖርት አውታር አጠቃላይ የኮንትራት ካርድ (Generalabonnement) አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። እስከ 6 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች በነጻ ይጓዛሉ። ዕድሜያቸው እስከ 16 ዓመት ድረስ የታዳጊ ወጣቶች ወይም የልጆች የጋራ የጉዞ ካርድ ካላቸው፣ ከወላጆቻቸው ወይም ከአያቶቻቸው ጋር በነፃ ይጓዛሉ። የቲኬቶች እና የደንበኝነት ምዝገባ ካርድ መረጃ ከስዊዘርላንድ ፌዴራል የባቡር ኩባንያ (SBB) ወይም ከትራንስፖርት ኩባንያዎች ማግኘት ይቻላል፡፡

## የሰሜን ምዕራብ ስዊዘርላንድ የታሪፍ ማህበር TNW

የሰሜን ምዕራብ ስዊዘርላንድ የታሪፍ ማህበር በባዝል እና አካባቢው ለትኬቶች ልዩ ታሪፍ፣ የደንበኝነት ምዝገባዎች እና ዕለታዊ ትኬቶች ልዩ ዋጋ ይሰጣል። የTNW የመረብ አውታረ የሚገኙ አካባቢዎች በበርካታ ዞኖች የተከፈለ ነው። በሰሜናዊ ምዕራብ ስዊዘርላንድ ክልል በትራም፣ በአውቶቡስ እና በባቡር በተደጋጋሚ የሚጓዙ U-Abo ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። እና በድንበር አቅራቢያ ባሉ የውጭ ሀገራት ለሚጓዝ ሰው የተለየ ቲኬት ያስፈልገዋል።

## የኮምዩኑ ዕለታዊ ትኬቶች

በስዊዘርላንድ ውስጥ ረዘም ያለ ጉዞ ለማድረግ ካቀዱ፣ በብዙ ኮምዩኖች ዕለታዊ ቲኬት (Gemeindetageskarte) በቅናሽ ዋጋ ማግኘት ይችላሉ። ነገር ግን ቅናሹ የተገደበ ነው፣ ቲኬቱን አስቀድመው ሪዘርቭ ማድረግ አለብዎት። በዚህ ላይ መረጃ ከነዋሪዎች ምዝገባ ጽ/ቤት ወይም ከኮምዩኑ አስተዳደር ጽ/ቤት ሊገኝ ይችላል፡፡

## የሌሊት መስመሮች

ቅዳሜና እሁድ (ሌሊት ከአርብ እስከ ቅዳሜ ባሉት ምሽቶች እና ከቅዳሜ እስከ እሁድ ሌሊት) ትራሞች፣ አውቶቡሶች እና ባቡሮች በሌሊት በባዝል-ከተማ እና አካባቢው ይሰራሉ። ለTNW የሌሊት መስመሮች ተጠቃሚዎች ምንም ዓይነት ተጨማሪ ክፍያ አያስከፍልም።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/mobilitaet/zug-und-bus

# በብስክሌት / በእግር

በደንብ የተሻሻለው የሳይክል መንገድ ኔትወርክ ምስጋና ይግባውና በBasel-Stadt ካንቶን ውስጥ ብስክሌት መንዳት በጣም ደስ የሚል ነው። ብዙ ሰራተኞች ወደ ሥራ ለመግባት ብስክሌቶችን ይጠቀማሉ። ለእግረኞች እና ለተጓዦች ልዩ የእግር እና የእግር ጉዞ መንገዶች አሉ፡፡

## በእግር ወይም በብስክሌት (በቬሎ).መጓዝ

ባዝል-ከተማ Basel-Stadt ለሳይክል ነጂዎች እና ለእግረኞች ማራኪ እና በተለይም በአንፃራዊነት ደህንነቱ የተጠበቀ ነው። በዚህም ምክንያት ለአጭር ርቀቶች ብዙዎቹ መኪናቸውን ትተው ይሄዳሉ። በብዙ ቦታዎች ልዩ የብስክሌት መስመሮች ወይም የብስክሌት መንገዶች አሉ። በእግረኛ ማቋረጫ ላይ ካሉት ተሽከርካሪዎች ሁል ጊዜ እግረኞች ቅድሚያ አላቸው። (መንገዱን ሲያቋርጡ በትራፊክ መብራት ካልያዛቸው በስተቀር) ። የBasel-Stadt ካንቶን ብዙ የሚያማምሩ የእግር እና የእግር ጉዞ መንገዶችን ያቀርባል፣ እነሱም በትርፍ ጊዜ በደንብ መጎብኘት ያለባቸው ናቸው። የእግር ጉዞ መንገዶች ዱካዎችን ለመለየት በቢጫ ምልክት ይደረግባቸዋል።

## ህጎች ብስክሌት ለሚነዱ

በስዊዘርላንድ ውስጥ ብስክሌት ለመንዳት ልዩ ፈቃድ ወይም ፈተና አያስፈልግዎትም። አጠቃላይ የትራፊክ ደንቦች እንደ መኪና ሾፌሮች ተመሳሳይ ናቸው። ልዩ የብስክሌት መንገዶች መንገዶች ወይም መስመሮች ካሉ፣ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው። ብስክሌቱ ለመንገድ ብቁ መሆን አለበት (ሁለት ጥሩ ፍሬኖች፣ ደወል፣ አንጸባራቂ ከፊት እና ከኋላ እና በፔዳል ላይ፣ የፊት እና የኋላ መብራቶች) ። የራስ ቁር የመልበስ ግዴታ የለበትም ፣ ነገር ግን የራስ ቁር /ሔልም/ ይመከራል። ብስክሌተኞች ለጉዳት (በሰዎች ወይም በንብረት ላይ) ተጠያቂ ስለሚሆኑ በእርግጠኝነት የግል የ3ኛ ወገን የመድን ዋስትና መግባት አለባቸው።

## ብስክሌት መንዳት መማር

ብስክሌት መንዳት መማር ከፈለጉ ኮርስ መውሰድ ይችላሉ። ኮርሶች የሚቀርቡት በፕሮ ቬሎ ማህበር ነው። ለስደተኞች አልፎ አልፎ ልዩ ኮርሶች አሉ። ርካሽ ያገለገሉ ብስክሌቶች በቬሎ ገበያ ላይ (Velobörsen) ይገኛሉ።

## የብስክሌት መጓጓዣ

በባቡር ወይም በአውቶቡስ ብስክሌት ለመውሰድ የፈለገ፣ ልዩ ትኬት ያስፈልገዋል። ብስክሌት ለመውሰድ ሁልጊዜ እና በሁሉም ቦታ ላይ አይቻልም። አንዳንድ ግዜ በባቡር በቅድሚያ ቦታ ሪዘርቭ ማድረግ ማዘዝ ያስፈልጋል።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/mobilitaet/fahrrad--zu-fuss

# መኪና / ሞተር ሳይክል

በስዊዘርላንድ በደንብ የተገነባ የመንገድ አውታር አለ። የአብዛኞቹ መንገዶች አጠቃቀም ከክፍያ ነፃ ነው። የትራፊክ ደንቦች በጣም አስፈላጊ ናቸው፤ እነዚህ ካልተተገበሩ ቅጣቱ ከፍተኛ ነው፡፡

## የትራፊክ ደንቦች

የትራፊክ ደንቦች በስዊዘርላንድ ውስጥ ላሉ መኪና አሽከርካሪዎች በጣም አስፈላጊ ናቸው። ቅጣቱ ከሌሎች አገሮች ጋር ሲወዳደር በጣም ከፍተኛ ነው። በጣም ከባድ በሆኑ የደንቦች መጣስ የመንጃ ፈቃዱን ወደ መነጠቅ ሊያመራ ይችላል፡፡
አንዳንድ አስፈላጊ ህጎች:

- በከተማ ውስጥ ከፍተኛው ፍጥነት: 50 ኪሜ / በሰዓት- ከከተማ ውጭ፡ 80 ኪሜ በሰዓት፣ ሀይዌይ፡ 100 ኪሜ በሰአት፣ አውራ ጎዳና፡ 120 ኪሜ በሰአት
- በአውራ ጎዳና፡ ላይ በቀኝ በኩል ማለፍ የተከለከለ ነው። በግራ በኩል ወይም በመካከለኛው መስመር ላይ በመስመር ኮሎን ከተፈጠረ፣ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ በቀኝ በኩል ማለፍ ይፈቀዳል።
- ብርሃን በቀትር መብራት አለበት፤
- በመኪና ውስጥ ያለ ሰው ሁሉ መታጠቅ አለበት።
- ልጆች በህጻን መቀመጫ ውስጥ መሆን አለባቸው (እስከ 12 ዓመት ወይም 150 ሴንቲሜትር ቁመት ድረስ)
- በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ስልክ መደወል የሚፈቀደው ከእጅ ነጻ በሆነ ስርዓት ብቻ ነው።
- በአልኮል ወይም በአደንዛዥ እጽ ተጽዕኖ ስር ሆኖ ማሽከርከር የሚያስቀጣ ወንጀል ነው (የአልኮል ገደብ 0.5)
- በእግረኛ ማቋረጫ ላይ ያሉ እግረኞች ሁልጊዜ ቅድሚያ አላቸው (ማቋረጡ በትራፊክ መብራቶች ካልተመራ በስተቀር)

## የመንገድ ግብር

መንገዶቹ በኮንፌዴሬሽን፣ በካንቶኖች እና በማዘጋጃ ቤቶች የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ናቸው። የመንገዶቹ አጠቃቀም ከክፍያ ነጻ ነው። ልዩ ሁኔታዎች ፈጣን አውራ ጎዳናዎች ናቸው።፡ ፈጣን አውራ ጎዳናዎች መጠቀም የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ቪግኔት (Vignette) በየዓመቱ መግዛት አለበት። ይህ በንፋስ መከላከያው መስተዋት ላይ መለጠፍ አለበት። ቪንቴቶቹ በነዳጅ ማደያዎች፣ በፖስታ ቤት ወይም በመንገድ ትራፊክ ቢሮዎች ይገኛሉ።

## ኢንሹራንስ

በስዊዘርላንድ ውስጥ የመድን ዋስትና ያላቸው የሞተር ተሽከርካሪዎች ብቻ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉት። የሞተር ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን መድን ዋስትና (Motorfahrzeug-Haftpflichtversicherung) በተለያዩ የግል ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ይሰጣል። ኢንሹራንሱ በንብረት እና በተሽከርካሪ ላይ በተሽከርካሪ ጉዳት ለደረሰባቸው ይከፍላል።. በራስዎ መኪና ላይ ለሚደርስ ጉዳት የተለያዩ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ አጠቃላይ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎችም (Kaskoversicherungen) አሉ። ማሳሰቢያ፡- አንድ ሰው በከባድ ቸልተኝነት አደጋ ካደረሰ፣ ኢንሹራንሱ ላይከፍል ይችላል (ለምሳሌ በአልኮል መጠጥ ወይም በአደንዛዥ እፅ ተጽዕኖ ስር ማሽከርከር)፣ የሞተር ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን መድን ዋስትና_፣ ከግል ከ3ኛ ወገን መድን ዋስትና ውስጥ አይካተትም።

## የሞተር ተሽከርካሪ ከውጭ አገር ማስመጣት

ሞተር ተሽከርካሪዎችን በቋሚነት ወደ ስዊዘርላንድ ማስገባት ከፈለጉ በጉምሩክ ቢሮ መመዝገብ እና ማስቀረጥ አለብዎት። የሚያስገቡት ተሽከርካሪ ቴክኒካዊ ፍተሻ ማድረግ አለበት። የሞተር ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን መድን ዋስትና፣ የስዊስ ተሽከርካሪ ምዝገባ ሰነድ እና የስዊዝ ታርጋ ቁጥር ያስፈልግዎታል። ከBasel-Stadt (Motorfahrzeugkontrolle) የሞተር ተሽከርካሪ መቆጣጠሪያ የበለጠ ዝርዝር መረጃ ማግኘት ይቻላል።

## መኪና መጋራት

የመኪና መጋራት ማለት ብዙ ሰዎች በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ መኪኖችን አብረው ይጠቀማሉ ማለት ነው። የመኪና ማጋሪያ ድርጅት ተሽከርካሪዎች ብዙውን ጊዜ በተከራዩ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ውስጥ ናቸው፣ እና በቅድሚያ በመስመር በኦን ላይን ወይም በመተግበሪያ በኩል ይታዘዛሉ። ቦታዎቹ ብዙውን ጊዜ በሕዝብ ማመላለሻ ማዕከሎች (ለምሳሌ ባቡር ጣቢያዎች፣ ትራም መገናኛዎች፣ የአውቶቡስ መስመሮች የመጨረሻ ጣቢያዎች) ናቸው። መጋራቱ ከመኪና ኪራይ የሚለየው ተሽከርካሪውን ለአጭር ጊዜ መጠቀም መቻሉ ነው፣ ለምሳሌ በሰዓት፣

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/mobilitaet/auto--motorrad

# የመንጃ ፍቃድ

በስዊዘርላንድ ውስጥ መኪና ወይም ሞተር ሳይክል ለመንዳት ሕጋዊ የመንጃ ፍቃድ ያስፈልግዎታል። ወደ ስዊዘርላንድ ከመጡ በኋላ የውጭ አገር የመንጃ ፈቃዶች መቀየር አለባቸው።

## የውጭ አገር መንጃ ፍቃድ

ወደ ስዊዘርላንድ የሚመጣ ሰው እና መንጃ ፍቃድ ያለው ማንኛውም ሰው በ12 ወራት ውስጥ ወደ ስዊዘርላንድ መንጃ ፍቃድ (Führerausweis) ማስቀየር አለበት። ይህንን ለማድረግ በ Basel-Stadt የሞተር ተሽከርካሪ መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት (Motorfahrzeugkontrolle) ማመልከቻ ማቅረብ አለበት። የመንጃ ፈቃዱ እንደወጣበት አገር ይለያያል፣ ለመለወጥ እንደሁኔታው የተለያዩ ደንቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ። የፍተሻ መንዳት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፣ ወይም ነጂው /አመልካቹ/ የስዊስ ቲዎሪ ፈተናን ማለፍ አለበት። ይህንን በሚመለከት የባዝል-ከተማ Basel-Stadt የሞተር ተሽከርካሪ መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል።.

## የመንዳት ፈተና

በስዊዘርላንድ የመንጃ ፍቃድ ለማግኘት፣ ፈተና አስፈላጊ ነው። የመንዳት ፈተናው የንድፈ ሃሳባዊ እና ተግባራዊ ክፍልን ያካትታል። ከ17 አመት በላይ የሆኑ ሰዎች ብቻ ፈተናውን እንዲወስዱ ይፈቀላቸዋል። የሞተር ተሽከርካሪ መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ስለ መስፈርቶቹ እና ስለ ትክክለኛው አሰራር መረጃ ይሰጣል። ለጭነት መኪናዎች፣ አውቶቡሶች እና ታክሲዎች ለማሽከርከር ልዩ ፈተናዎች ያስፈልጋሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/mobilitaet/fuehrerausweis